# በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የይግባኝ ፍርድ ቤት
# ስለይግባኝ ሽምግልና በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ሽምግልና ምንድን ነው?

በይግባኝ ፍርድ ቤት የሚካሄደው የሽምግልና ሂደት ይፋዊ ያልሆነ፣ ምስጢራዊ ሂደት ሲሆን፣ በሽምግልናው ሂደት የሚሳተፉ ወገኖች በገለልተኛ ሽምጋይ አማካኝነት ጉዳያቸውን ይፈታሉ፤ ሽምጋዩ ለጉዳዩ በድርድር ላይ የተመሠረተ መፍትሄ ለመሻት ተሸምጋዮችን እንዲያግዙ በፍርድ ቤት ሥልጠና የተሰጣቸው እና የተመረጡ ናቸው፡፡ የሽምጋዩ ሚና በተሸምጋይ ወገኖች ማካከል ግልጽ የሆነ የሃሳብ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ እና ያሏቸውን አማራጮች ማሳወቅ ሲሆን፣ ተሸምጋይ ወገኖች ጉዳያቸውን በድርድር መፍታት ካልቻሉ፣ ሽምጋዩ በይግባኝ ፍርድ ቤት ክርክር የሚደረግባቸው ነጥቦች ተገቢው ይዘት እንዲኖራቸው እና አንዳንዶቹም እንዲሰረዙ ያግዛሉ፡፡

ተሸምጋይ ወገኖች፣ ጠበቆቻቸው እና ሌሎች አለመግባባቶችን ለመፍታት ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ጊዜያት ከሽማግሌው ጋር ይገናኛሉ፡፡ የጋራ ውይይት ከተደረገ በኋላ ሽምጋዩ ከእያንዳንዱ ወገን ጋር ለየብቻ ተገናኝተው ይነጋገራሉ፡፡ በጋራ እና በተናጠል ውይይት ጊዜ ተሳታፊዎች ፈቃደኞች እስከሆኑ ድረስ በነጻነት ተሳትፎ ማድረግ ይችላሉ፡፡ በአብዛኞቹ የሽምግልና ክፍለ ጊዜያት ተሳታፊዎች በአካል የሚገኙ ቢሆንም፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች ተሸምጋይ ወገኖች በስልክ እንዲገናኙ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

ጉዳዩ በድርድር የሚፈታ መሆኑን፣ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ በምን መልኩ እንደሚፈታ የመወሰኑ ድርሻ የተሸምጋይ ወገኖች ብቻ ነው፡፡ ሽምጋዩ ውሳኔ ወይም ስለጉዳዩ አፈታት ትዕዛዝ አይሰጡም፡፡ ተሸምጋይ ወገኖች ከስምምነት መድረስ ካልቻሉ፣ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍትሔ ያገኛል፡፡

## የሽምግልና ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

የይግባኝ ሂደት ውድ እና ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ተሸምጋይ ወገኖች በይግባኝ ሂደት ለተጨማሪ ወጪ ሳይዳረጉ፣ የሥነ ልቦና ውጥረትም ሳይደርስባቸው በሽምግልና ሂደት ለጉዳያቸው መፍትሔ ማግኘት ከቻሉ፣ ጊዜ እና ገንዘብ መቆጠብ እና በተራዘመ ክርክር ምክንያት የሚደርስባቸውን ጭንቀት ማስቀረት ይችላሉ፡፡

ክርክር ሁል ጊዜም ቢሆን በተከራካሪ ወገኖች ላይ የተወሰነ ስጋት ማስከተሉ የማይቀር ነው፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩን በራሳቸው ከመፍታት ይልቅ ለፍርድ ቤት የሚያስተላልፉ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ሽምግልና በአለመግባባቱ ላይ የመወሰኑን ሥልጣን ለእነርሱ ስለሚሰጣቸው የተገለጸውን ስጋት ለመቀነስ ያስችላቸዋል፡፡ ተሸምጋዮቹም አለመግባባቱ በምን መልኩ እንደሚፈታ ራሳቸው ይወስናሉ፡፡

በሽምግልና አማካኝነት ተሸምጋዮቹ በይግባኝ ሂደት ቢያልፉ የማያገኟቸውን ዓይነት ልዩ ልዩ አማራጮች ተጠቅመው አለመግባባቱን ለመፍታት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ተሸምጋዮቹ ወገኖች

በሽምግልና አማካኝነት የሚደርሱበት ስምምነት በጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ሄዶ ከሚገኘው ውጤት ይልቅ አጠቃላይ፣ አዳዲስ መንገዶች የሚፈተሹበት እና ለእነርሱም አመርቂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## በሽምግልና ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች ምን ዓይነቶቹ ናቸው?

ሁሉም ወገኖች በጠበቆቻቸው የተወከሉባቸው የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች በሽምግልና ሊፈቱ የሚችሉ ናቸው፤ ከእነርሱም መካከል፡- የውርስ ጉዳዮች፣ የጋብቻ የጋራ ንብረት እና የልጆች ሞግዚትነት እና አስተዳደራዊ የይግባኝ ጉዳዮች ይገኙባቸዋል፡፡ በሽምግልና ሊፈቱ ከማይችሉ ጉዳዮች መካከል፡- የልጆች/ወጣቶች ጉዳይ የፍርድ ቤት ጉዳዮች፣ የጠበቆች ፈቃድ፣ ፈቃድ ሳይኖር የሕግ አገልግሎት መስጠት፣ በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጸም የኃይል ድርጊት፣ የሕጻናት ጥቃት እና ኃላፊነትን አለመወጣት፣ የወላጅነት መብቶች መቋረጥ፣ ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻ እና ሞግዚትነት ጉዳዮች ይገኙባቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የወንጀል ጉዳዮች በሽምግልና የሚቋጩ አይደሉም፡፡

## ባለጉዳዮች በፍርድ ቤት ራሳቸውን ወክለው የሚቀርቡባቸው ማለትም ቢያንስ አንዱ ወገን ያለጠበቃ የሚቀርብበት ጉዳይ በሽምግልና ሊፈታ ይችላልን?

አይቻልም፣ ምክንያቱም ጉዳዩ በሽምግልና እንዲፈታ ሁሉም ወገኖች በጠበቆቻቸው መወከል አለባቸው፡፡

## በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የይግባኝ ፍርድ ቤት ሽምግልና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው?

ሽምግልና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው፤ ይህም ማለት ተሸምጋዮቹ ወገኖች በይግባኝ የሚቀርበውን ጉዳይ በሽምግልና ለመፍታት እና ለእርሱም መነሻ ለሆነው ምክንያት መፍትሄ ለመስጠት የመወሰን ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

ሆኖም ግን አንዱ ወገን በሽምግልና ሂደት ውስጥ የሚሳተፍ መሆኑ ወይም አለመሆኑ በፈቃደኝነት የሚወሰን ነገር ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የተሸምጋዮቹ ወገኖች ጠበቆች ምክር የሚጠየቁ ቢሆንም እንኳን፣ አንድ ጉዳይ በሽምግልና እንዲታይ መመራቱን የሚወስነው ፍርድ ቤቱ ነው፡፡

አንድ ጉዳይ በሽምግልና እንዲታይ ከተመራ በኋላ፣ ተከራካሪዎች በሽምግልናው ክፍለ ጊዜ መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተሸምጋዮች በዚህ ሂደት ውስጥ በቅን ልቦና ተሳትፎ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፤ ለሽምግልና ሂደትም የሚያውሉትን ጊዜ በውጤታማነት እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ፡፡

## በሽምግልናው መሳተፍ ያለበት ማነው?

በሽምግልና ቀጠሮ ወቅት ተሸምጋዮች፣ ጠበቆች እና ማናቸውም ተሸምጋይ ያልሆነ ነገር ግን ጉዳዩን ለመፍታት ሥልጣን ያለው ሰው መገኘት አለበት፡፡ አንድ ተሸምጋይ ወይም ጠበቃ በሽምግልና መርሃ ግብር ሠራተኞች አስቀድሞ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ካልሆነ በስተቀር በሽምግልና ቀጠሮ ቢቀሩ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሊጥልባቸው ይችላል፡፡

**የሽምግልና ሂደቱ ምስጢራዊ ነውን?**

በሕግ እንደተደነገገው ካልሆነ በስተቀር፣ የሽምግልና ሒደት ተሳታፊዎች እና የሽምግልና መርሃ ግብር ሠራተኞች ከሽምግልናው ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በምስጢር መያዝ አለባቸው፡፡ ተሳታፊዎችም በድርድሮቹ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳታፊ ከሆኑ ሰዎች ጋር መረጃ ሊለዋወጡ ይችላሉ፡፡

ሽምጋዮች ወይም የሽምግልና መርሃ ግብር ሠራተኞች ለፍርድ ቤቱ ሊገልጹ የሚችሉት የሚከተሉትን መረጃዎች ብቻ ነው፡- ሽምግልናው መካሄዱን ወይም መቋረጡን፤ ወደ መፍትሄ መድረስ መቻሉን፤ በሽምግልናው ሂደት ማን እንደተሳተፈ፤ በሁሉም የሽምግልናው ተሳታፊዎች በተፈረመ በጽሁፍ የተዘጋጀ የመፍትሄ ስምምነት ውስጥ የሚገኝ መረጃ፡፡

በተጨማሪም፣ በሽምግልናው ሂደት በአንድ ሰው ላይ ጥቃት፣ ኃላፊነትን አለመወጣት፣ መጣል ወይም መተው ወይም ብዝበዛ የተፈጸመ መሆኑን የሚያመላክቱ መረጃዎችን ካገኙ ሽምጋዩ መረጃዎቹን ሰዎችን ከእንደዚህ ዓይነት ድርጊት ለመጠበቅ ኃላፊነት ለተሰጣቸው ኤጀንሲዎች መግለጽ ይችላሉ፡፡

**ጉዳይዎ በሽምግልና እንዲታይ መመረጡ በክርክር ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ ላይ የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው?**

በአብዛኛው በሽምግልና ለመታየት የተመረጡ ጉዳዮች፣ የይግባኝ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ፣ ለምሳሌ የሥር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንዲዘጋጅ ትዕዛዝ የመስጠት ግዴታ እና የፍሬ ነገር እና የሕግ መከራከሪያ ነጥቦች ማቅረቢያ ጊዜ የሽምግልናው ሂደት እስኪናቀቅ ድረስ መቆጠራቸው ይቆማል፡፡ ጉዳዩ በሽምግልና መፈታት ካልቻለ ግን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ በድጋሚ መቆጠር ይጀምራል፡፡

**ተከራካሪ ወገኖች ወይም ጠበቆች ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ መጠየቅ ይችላሉ?**

አዎ፣ ጉዳዩ በሽምግልና ሊታይ የሚችል ከሆነ መጠየቅ ይቻላል፡፡ የሽምግልና መርሃ ግብር አስተባባሪ ከሆኑት ከስኮቲ ሬይድ (Jennifer M. Gartlan) ጋር በስልክ ቁጥር 202-879-9936 ወይም በኢሜል mediation@dcappeals.gov በመገናኘት ጥያቄው ሊቀርብ ይችላል፡፡

**ተከራካሪዎች ጉዳያቸውን የሚሸመግሉላቸውን ሰው መምረጥ ይችላሉ?**

ሽምጋዮች የሚመረጡት የእያንዳንዱን ጉዳይ ሁኔታ እና የሽምጋዩን ሙያዊ ብቃት በማጤን በፍርድ ቤት ነው፡፡

**ለሽምግልና የሚከፈል ክፍያ አለን?**

የለም፤ የሽምግልና መርሃ ግብር ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይጠየቅ በፍርድ ቤቱ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡

**ሽምግልናዎች የሚካሄዱት የት ነው?**

በሌላ መልኩ መምሪያ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ሽምግልናዎች የሚካሄዱት በ510 4th St. N.W., 2nd Floor, Washington, D.C. 20001 ነው፡፡